# የፀሎት እህትማማችነት

ሁላችሁም የፀሎት እህትማማችነት ለሚባለው አገልግሎት ተጋብዛችኋል!!

ይህ አገልግሎት በክርስቶስ እህትማማቾች የሆንነው ሴቶች እርስ በእርሳችን እንድንተናነፅና ያለንን እንድንከፋፈል እድል ከመስጠቱም በላይ ለሌሎች እንክብካቤ ማድረግን እና ፍቅርንም የሚያስተምር ነው።

እያንዳንዷ እህት ከአንዲት ሌላ እህት ጋራ ትመደባለች። የምናደርገው ነገር ቢኖር ለተመደበችልን እህት መፀለይና ያቺን እህት ማበረታታት ነው።

በየዕለቱ የሚፀልይልንና አልፎ አልፎ የማበረታቻ ቃልን የሚልክልንን ሰው ማግኘት ትልቅ ነገር ነው።

የተሰጡንን እህቶች ስም በሚስጥር እንይዛለን። የተመደበላችሁን እህት ለራሷም ሆነ ለሌሎች ሰዎች አትናገሩም። መገመት ትችላላችሁ ከሚልኩላችሁ ቃልና አንዳንድ ሁኔታ።

ነገር ግን ከተወሰነው ጊዜ በፊት ራሳችሁን አትገልጡም። በአመቱ መጨረሻ ላይ የፀሎት እህትማማቾቹ እነማን እንደነበሩ ይገለፃል።

## የአገልግሎቱ ተሳታፊዎች ሃላፊነት

**1- ቃልኪዳን እንደገባችሁ እወቁ**

የተመደበችላችሁ እህት ከእናንተ የፀሎት ድጋፍ እና ማበረታታ ለማግኘት እንደምትጠብቃችሁ እወቁ።

**2- በየእለቱ ለተሰጣችሁ እህት ፀልዩ**

በተቻላችሁ መጠን የሚያስፈልጋትን የፀሎት ርዕስ እወቁና በዚያ ላይ ፀልዩላት።

**3- ያቺን እህት ለመተዋወቅ ሞክሩ**

በተዘዋዋሪ መንገድ የምትወደውንና የምትጠላውን ነገር ለማወቅ ሞክሩ። በአጠቃላይ ስለእርሷ ለማወቅ ሞክሩ።

**4- ለእህታችሁ አበረታች ሁኑ**

ካርድም ይሁን አጭር የማበረታቻ ጥቅስ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ላኩላት።

**5- የእህታችሁን ልዩ ቀን አስታውሱ**

የልደት ቀን፤ የጋብቻ ቀን፤ የትምህርት ቤት ምርቃት፤ አዲስ ስራ ማግኘት፤ ልጅ መውለድ፤ በእነዚህ ጊዜያት የደስታ

መግለጫ ካርድ መላክ አትርሱ።

**6- ሚስጥር ጠብቁ**

ከማን ጋራ እንደተመደባችሁ ለማንም አትናገሩ የምትልኩትን ካርድም ይሁን ደብዳቤ ስትልኩ ማንም እንዳያያችሁ።

7- ፕሮግራሙን መቀጠል ካልቻላችሁ ለእህቶች ህብረት አስታውቁ።

# ማሳሰቢያ

1) አነስተኛ ነገር ለተመደበችላችሁ እህት አልፎ አልፎ መላክ ትችላላችሁ። ነገር ግን በዓመቱ መጨረሻ ላይ ሚስጥሩ ሲገለፅ ለልደት በአል (christmas) ጊዜ ትንሽ ዝግጅት እናደርግና ለተመደበችልን እህት በግልፅ ማንነታችንን ገልፀን መለስተኛ ስጦታ እንሰጣታለን።

2) ቢያንስ በየወሩ የማበረታቻ ቃል መላክ አትርሱ።

በዚህ ፕሮግራም በጌታ የሆኑ እህቶቻችሁን ከመተዋወቃችሁም በላይ ጥሩ ደስ የሚያሰኝ (Fun) ጊዜ ሊኖራችሁ ይችላል። የምትልኩት የማበረታቻ ቃል ጌታ ያችን እህት የሚነካበት ሊሆን ይችላል።

"በወቅቱ የተሰጠ ቃል ምንኛ መልካም ነው" ምሳሌ፤ 15፡ 23

በየቀኑ ለተመደበችልን እህት ስንፀልይ እኛን ራሳችንን ከማበረታታቱም በላይ ከጌታም ዋጋን እናገኝበታለን።

ልባም ሴት የእህቶች አገልግሎት
የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን በሂውስተን